## ግልፅ ደብዳቤ ለፕሬፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
## እውነትን በወርዷና በቁመቷ ልክ ማን ይናገራት?!

**ከእውቀቱ ሰናይ(አዲስ አበባ)**

የተከበሩ ፕሬፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ይሄን ደብዳቤ ለመፃፍ የተነሣሁት በተከታታይ በጋዜጣ ላይ የሰጡት ቃለ መጠይቅ ስላስገረመኝና <u>«ለመሆኑ እኛ ሀገር እውነትን በወርዷና በቁመቷ ልክ ሊናገራት የሚችል የሀገር ሽማግሌ ይኖር ይሆን?»</u> የሚል ጥያቄን በውስጤ ስላጫረብኝ ነው።

ሆኖም ከዚሁ ጋር አያይዤ ልገልፅልዎት የምፈልገው ለእርስዎ ከፍተኛ ክብር ያለኝ ወጣትም መሆኔን ነው። በዚህ እድሜዎ ለዚህች ምስኪን አገር በአቅምዎት ለማድረግ እየሞከሩት ያለውን አስተዋፅኦ በታላቅ አድናቆት አስተውለዋለሁ።
ሆኖም ሰሞኑን እየሰጡት ያለው መግለጫና ቃለ መጠይቅ እኝህ ሰውን አላቃቸውም ማለት ነበር ብዬ እራሴን እስክጠይቅ አድርሶኛል። ለምን ወደዚህ ጥያቄ እንዳመራሁም አንድ በአንድ እንደሚከተለው እገልፅልዎታለሁ። እርስዎም እነዚህን ነጥቦች እንደገና ይመርምሯቸዋል ብዬ አስባለሁ፤

1ኛ. <u>የፖለቲካ ርዕዮተ አለምዎት ሌላ እርስዎ የመሰረቱት ፓርቲ ርዕዮተ አለም ሌላ</u> ታህሳስ 19/2000 ዓ.ም. «ለአዲስ ነገር ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ «እኔ ሶሻሊስት ነኝ። ኮሚኒስት ግን አይደለሁም።» ሲሉ በሶሻሊስት ዲሞክራሲ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅምና ብዙሃኑን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ እንዴ ግምት ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል ገልፀዋል።

በእዚህ እውነት እኔም እስማማለሁ። ለኢትዮጵያ ሙጭጭ ካለ ሊብራል ዲሞክራሲ ይልቅ ሶሻል ዲሞክራሲ በተሻለ ህዝቧን ለመጥቀም ያግዛ ል ብዬ እገምታለሁ።
የገረመኝ እና እርስዋንም ልጠይቅዎት ያነሳሳኝ ጉዳይ ሌላ ነው። እርስዎ በገለፃዎ መሠረት ከቅንጅት ሰዎች ጋር ሆነው ሊብራል ዲሞክራሲን ለማራመድ ያነሳሳዎት ሁኔታዎች እስኪጠሩ እና ሰዎች እስኪገነዘቡት ብለው ነው።

እንደ እርስዎ አይነት ትልቅ የሀገሪቱ ምሁር እና የማህበራዊ ሳይንስ ሊቅ የርዕዮተ አለም ጠቀሜታ እንዴት አንሶ ሊታየዎ ይችላል? በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የተከሰተውና ሀገሪቷን ስንኩል አድርጎት የቀረውና አሁንም እያተራመሳት ያለው ሀቅ የነጠረ የርዕዮተ አለምና ሀገራዊ ፍልስፍናን ከስሜት እና በአንድ ሰሞን ከሚከሰት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሆያ ሆዬ በፀዳ ሁኔታ አጥንቶ፣ ተንትኖ፣ እና ቀምሮ የሚቀርብ ምሁርና ምሁራን መጥፋቱ ነው።

ከዚህም በመቀጠል ይሄን የተጠና፣ የተተነተነ እና ተቀመረ ርዕዮተ አለምና ሀገራዊ ፍልስፍና ወደ ፓርቲ ለውጦ በማህበረ-ባህላችን እና በሀገሪቱ ህዝብ ስነባህሪ ውስጥ የሚያሰርፅ አካል መጥፋቱ ነው። እኔ ከቅንጅት የአንድ ሰሞን ድል በላይ እና በምርጫ የፓርላማን ወንበሮች ከመቆጣጠር በዘለለ ሁኔታ ይሄ ጉዳይ ለታላቂቱ ሀገራችን ቀጣይ፣ ሰላማዊና የሰከነ ሁለ አቀፍ ልማት የበለጠ ዋጋና እሴት አለው ብዬ አስባለሁ። በዚህ ዙሪያ ነገሩን በጥልቀት የሚመረምሩም ወገኖች ተመሳሳይ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ብዬ አስባለሁ።

ይሄንንም ቢያንስ አንድ እርምጃ በሀቅ እና በእውነት ላይ ቆሞ ሊጀምረው የሚገባ የሀገሪቱ ምሁር መሆን አለበት። እርስዎ ደግሞ ከእነዚህ ምሁራን ቀዳሚ መሆን ነበረብዎት።

የፖለቲካ ሳይንቲስቶች መርህና ርዕዮተ አለም የሌለው ፖለቲካ ዝም ብሎ መንጫጫት ነው ይላሉ። እርስዎ በውስጥዎት ለዚህች ሀገር ሶሻል ዲሞክራሲ እንደሚበጃት እያወቁና እያመኑ ይሄን የሚያስፈፅም ፓርቲን ከመሰል ምሁራን ጋር በመሆን ከመመስረት ይቅል ሰዎች ሰብሰብ ወዳሉበትና ሞቅ ሞቅ ወዳለበት ቡድን ውስጥ ዝም ብለው ተቀላቀሉና "walk the walk, talk the talk" እንደሚባለው ሊብራል ዲሞክራሲን ከሚሰብኩና ከሚተገብሩ ሰዎች ጋር ተሰለፉ። ይሄ ምን ማለት ነው? ይሄስ ለእኛ ለወጣቶች ምን ያስተምራል? የሞቀበትና የደመቀበትን ቡድን ሁሉ መቀላቀል?

ለመሆኑ አንድ ምሁር ማስቀደም ያለበት የእውነት ሀሳቡን እና የሚያምንበትን ርዕዮተ አለምን ነው ወይስ እርስዎ እንዳደረጉት የሰዎችን ስብስብ?

የዚህች ሀገር ጥፋት እና በዘፈቀደ መመራት የሚጀምረው ምሁሮቿ/በተለይም እንደ እርስዎ ፖለቲካ ውስጥ ያሉት/ ለመርህ መቆም በአለመቻላቸው ነው። በሁኔታዎች ውስጥ የሚተጣጠፉና ሁኔታው ሲያልፍ ግን «ብዬ ነበር የሚሉ መርህ የሌላቸው ሆነው መገኘታቸው ነው። ልክ እርስዎ ሰሞኑን እንደነገሩን ድንገት ብድግ ይሉና እኔ እኮ ወትሮም እንዲህ ነበርኩ ብለውን ቁጭ ይላሉ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለመሆኑ ቅንጅት ሆኖለት አገር ለመምራት ቢጀምር ኖሮ በየትኛው ርዕዮተ አለም አገሪቷ እንድትመራ ይፈቅዱ ነበር? በሊብራል ዲሞክራሲ? ወይስ ልክ አገሪቱን ለመመራት እንደጀመራችሁ የለም ከሊብራል ዲሞክራሲ ወደ ሶሻል ዲሞክራሲ እንለወጥ ብለው በፓርቲው ውስጥ ቅስቀሳና ሎቢ በመጀመር የፓርቲ ክፍፍል ይፈጥሩ ነበር? ነው ወይስ በማያምኑበት ርዕዮተ አለም የሚመራን መንግስት እየደገፉ ይቀጥሉ ነበር? ለመሆኑ የሚያምኑበት የሚኖሩለት ርዕዮተ አለምና መርህ ምንድን ነው? ምሁር እኮ የህሊና ልዕልና ላይ የደረሰ ማለት ነው ሲሉ አንድ ወቅት የፃፉትን ፅንሰ ሀሳብ እራስዎት ላይ ሲደርስ ለምን ተግባራዊ ማድረግ አቃትዎት? መርህና ርዕዮተ አለም አለዎት?

2ኛ. <u>የትሮትስኪ ትንታኔን ለምን ወደ ራሳችሁ ፓርቲ እውነት ሊመልሱት ሲሞክሩ እውነቱን ሸሹት?</u>

ለቃለ መጠይቁ በሰጡት መልስ «ሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና አባል የነበረው ትሮትስኪ የኮሚኒስት ፓርቲውን አካሄድ ተመልክቶ ስለአምባገነንነት አመጣጥ፣ አፈጣጠር ሲናገር የማዕከላዊ ኮሚቴ የሚለው ይፈጠርና ፓርቲውን ይተካዋል፡ ፓርቲው ዋና መሆኑ ይቀርና ማዕከላዊ ኮሚቴው ዋና ይሆናል፡፡ ከዚያ ደግሞ ፖሊት ቢሮ ወይንም የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ይፈጠርና ላዕላይ ምክር ቤት ወይንም ሴንትራል ኮሚቴ የሚለውን ዳር አውጥቶ ምንም ዋጋ የሌለው ያደርገዋል» ሲሉ አብራርተዋል፡፡ ይሄም እውነት ቅንጅት ውስጥ እንደተከሰተና ተጠያቂውም ፕሬዝዳንቱ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ የኔም ጥያቄ ይሄን ጉዳይ አስመልክቶ ነው፡፡

በዚሁ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዶ/ር ብርሃኑ ሎቢና ቅስቀሳ በማድረግ እነ ልደቱን እና ዶ/ር አለማየሁ ረዳን እንዲሁም በርካታ ትልልቅ ሰዎችን ከጨዋታ ውጭ በማድረግ የራሱን የመሳሳብ ቡድን ወ/ት ብርቱካንን፣ አቶ ኢዮኤልን፣ ዶ/ር ያዕቆብን እና ሌሎችንም ያስመረጠበት ሂደትና የስራ አመራሩን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች ለማስያዝ ያደረገውን እንቅስቃሴ የሚያስመሰግነው መሆኑን ገልፀውልናል፡፡ አያይዘውም አቶ ልደቱ ይሄን ቅስቀሳና ሎቢ ባለመስራቱ ወይም ሌሎች ወገኖች ቅስቀሳና ሎቢውን ባለመስራታቸው ሞኞች መሆናቸውን በሚያስተዛዝብ ሁኔታ ገልፀውልናል፡፡ ስለሆነም ተበለጡ ሲሉ ነግረውናል፡፡

ሲቀጥሉም ዶ/ር ብርሃኑ የመሳሳብ ቡድኑን የመሰረተው እና እያሰባሰበ የነበረው ከአምስት አመት በኋላ የሥልጣን ክፍተት እንደሚፈጠር ስለተረዳ ለዚያ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የፕሬዝዳንትነት ስልጣን እራሱን እያዘጋጀ ስለነበረ ነው፡፡ ሲሉ ጉዱን ግልብ አድርገው ይነግሩን እና መልሰው ይሄም መልካም አካሄድ ነበር ሲሉ አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ አይነት ንግግር ያደርጉልናል፡፡

ከላይ የትሮትስኪን ገለፃ ለኢ/ር ሀይሉ ሻውል ማጣጣያነት የጠጠቀሙበትን ፅንሰ ሀሳብና አደገኛ የአምባ ገነንነት አካሄድ ነው ያሉትን ስልት ወደ ብርሃኑ ሲያመጡት ደርሶ በሎቢ፣ በቅስቀሳና ስልጣንን የመያዝ መብት ሲሉ ሸፋፍነውት ያልፋሉ፡፡ ለዚህም እውነት ማሳያነት የሚከተለውን ሀቅ ያስተውሉት፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ያሰባሰበው የመሳሳብ ቡድን በእስር ቤት ጀምሮ በድርጅቱ ፕሬዝዳንት ላይ አምፆ ነበር፡፡

አስገራሚ ነገር ታዲያ ልክ ትሮትስኪ እንዳለው የስራ አመራሩ ላዕላይ ኮሚቴውን ከጨዋታ ውጭ ያደረገው ወዲያው ከዕስር እንደተፈታ ነበር፡፡ በወ/ት ብርቱካን የሚመራው ቡድን ያልታሰራችሁ አያገባችሁም በሚል ሰበብ ላዕላይ ኮሚቴውን ከጨዋታ ውጭ በማድረግና የፕሬዝዳንቱ በማጣጣል የራሱን እርምጃ ወሰደ፡፡ በዚህም ግልፅ እና የአደባባይ ፀብ ታወጀ፡፡ ይሄን ማን እና ለምን ጀመረው? ብለው በንፁህ ህሊና ከጠየቁ መልሱ የዶ/ር ብርሃኑ የመሳሳብ ቡድን ነው፡፡ ትሮትስኪ እንዳለው የዶ/ር ብርሃኑ ቡድን ሁሉን ነገር ተቆጣጥሬአለሁ ብሎ ሲያስብ (ከፕሬዝዳንቱ ቦታ በቀር) ላዕላይ ኮሚቴውን እና ፕሬዝዳንቱን መጫወቻ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡ ሲል ታጥቆ ገሀድ አመፅ ውስጥ ገባ፡፡

የኮሚኒስት ፓርቲ አካሄድን የተከተለውና ኮሚኒስታዊ የድርጅታዊ ስራን በመስራት የቅንጅት ፓርቲን በመዳፉ ለማስገባት የቋመጠው የእነ ወ/ት ብርቱካን ቡድን ሆኖ ሳለ እርስዎ በቃለ መጠይቅዎት በድፍረትና በአድሎአዊነት የአቶ ልደቱ ፓርቲ የሶሻሊስታዊና ኮሚኒስታዊ ቅኝነት የሚከተልን ነው፡፡ ሲሉ ኮነኑት፡፡ ይሄ እውነት ከእርስዎ ይጠበቃል?

በአንድ መልኩ በተግባር አቶ ልደቱ በራሱ ቡድን የቅንጅት ፓርቲን ለመቆጣጠር ወይም እራሱ ለመመረጥ ምንም አይነት ቅስቀሳና ሎቢ አለማድረጉንና ይሄም ስህተት እንደሆነ ነገሩን፡፡ በዚህም ሞኝ ስለሆነ በእነ ብርሃኑ እንደተበለጠ መሁከሩልን፡፡ ስለዚህም እንዴት ከፓርቲው እኩርፎ እንደወጣ ዘረዘሩልን፡፡
በሌላ በኩል ዶ/ር ብርሃኑና ቡድኑ ፓርቲውን በራሱ ሰዎች ለመቆጣጠር የሰራው ሎቢና ቅስቃሳ እንዴት መልካም እንደሆነ መሰከሩልን፡፡

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዘወር ብለው ደግሞ ግለሰቦች ወደ አምባገነንነት የሚሄዱት ትሮትስኪ እንዳለው ስራ አመራሩን፣ ፖሊት ቢሮውን በራሳቸው ቡድን ሲቆጣጠሩትና ላዕላይ ኮሚቴውን ከጨዋታ ውጭ ሲያደርጉት መሆኑን አብራሩልን::

ሆኖም ዶ/ር ብርሃኑና ቡድኑ እንዴት ወደ አምባገነንነት እያመሩ እንደነበርና ሆኖላቸው ቢሆን ኖሮም እንዴት ፓርቲውን ሙሉ ለሙሉ በራሳቸው መሰል ሰዎች ሊቆጣጠሩት እንደነበረ አይገልፁልንም:: ከዚያ ይልቅ ቅስቀሳና ሎቢ በፓርቲ ውስጥ የተለመደ አሰራር እንደሆነ አድበስብሰው ሊያሞኙን ይሞክራሉ::

አስገራሚው ነገር ታዲያ የኮሚኒስትና የሶሻሊስት ፓርቲን ስትራቴጅና ስልት እየተከተሉ ያሉት እነ ዶ/ር ብርሃኑና እነ ወ/ት ብርቱካን ሆነው ሳለ በመሣሣብ ፓርቲውን ሊወጡት ታጥቀው እንደተነሱ እያዉቁ እርስዎ ፍፁም በአድሎአዊነት ኢዴፓ መድህን (አቶ ልደቱን መሆኑ ነው) አካሄዱ ሁሉ ሶሻሊስትአዊና ኮሚኒስታዊ ነው ሲሉ መሰከሩልን:: እውነት እንዲህ ከምድሪቱ ትጥፋ?

እነ ዶ/ር ብርሃኑና ወ/ት ብርቱካን የመሰረቱት ቡድን ፍፁም አምባገነን ሆኖ መውጣቱ የሚታወቀው ታዲያ ዶ/ር ብርሃኑ ያለ ሥልጣኑ ፕሬዝዳንቱ የሰየሙትን ሲሽር ወ/ት ብርቱካን ላእላይ ኮሚቴውን ስላልታሰራችሁ ብላ ከስብሰባ ስታባርር፣ ኢ/ር ግዛቸው በአውሮፓና አሜሪካ ስልጣን ከፕሬዝዳንቱ ነጥቀን ለወጣቶቹ እንሰጣለን ሲል፣ እና የመሳሰሉ ህገወጥ አካሄዶችን ሲከተል መስተዋሉ ነው::

እርስዎን የሚያክል ትልቅ ያገር ሽማግሌ ታዲያ ይሄን መሰሉን ቡድን በህግ የሚመራ ይሉና ይጠሩታል:: ኢ/ር ሀይሉን እና በሳቸው የሚመራውን ወገን ደግሞ ህገወጥ ይሉታል:: ህግ ምንድን ነው? እንዴትስ ይተረጎማል? መቼስ ይሄ ለእርስዎ ይጠፋዎታል ብዬ አላስብም::

ሀሳብዎትን እና ወገንተኛንዎትን በማጠናከርም የኢ/ር ሀይሉን ወገን እየኮነኑ የእነ ወ/ት ብርቱካን ስህተትን ግን እያድበሰበሱ እና ማን እንደተናገረው እንኳን ሳይጠቅሱ በደፈናው «የታሰረና ያልታሰረ የሚል ነገር መጣ» ሲሉ ነገሩን አልዝበውና ወ/ት ብርቱካንን ከተጠያቂነት ነፃ ለማውጣት በሚያመችዎት መልክ ለመግለፅ ሲሞክሩ ሳስተውል እዚህ ሀገር ላይ እውነትን በቁመቷና በወርዷ ልክ ማን ይናገራት? ስል እራሴን ጠየቅሁ::

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

3ኛ. <u>ቀስተደመናን ፓርቲ ለምን ከደሙ ንጹህ ሊያደርጉት ይታገላሉ?</u>

በሀበሻ ባህል «የወለዱትን ሲስሙለት» የሚባል አባባል አለ። መቼስ እርስዎ ቀስተ ደመናን ከወለዱት ሰዎች አንዱ ነዎትና ይሄን ፓርቲ ሰዎች ሲካክቡት እና ሲያሞጋግሱት እንጂ ሲያጣጥሉት እና ሲኮንኑት ጭንቅ ሊሆንብዎት ይችል ይሆናል። ሆኖም ይሄን የምለዎት ታዲያ በሰብአዊ ስሜትዎት ወስጄ እንጂ በምሁራዊ ልዕለ ህሊናዎት ሰፍሬዎት አይደለም።

በምሁራዊ ልዕለ ህሊናዎት ስመዝንዎት ግን እውነትን እንደወረደች እንዲገልጿትና እንዲቀበሏት ነው። እርስዎም የሚያውቁትን አንድ የኢትዮጵያን ምርጥ ታሪክ ልንገርዎት ዛሬ ደብረብርሃን በሚባለው ከተማ ይኖር የነበረ ንጉስ እንዳይደረግ የከለከለውን ትዕዛዝ የገዛ ልጁ ጣሰው ትዕዛዙን የጣሰ ሰው ሞት ነበርና የሚበየንበት በዚህ ልጅም ላይ ንጉሱ ሞት በየነበት። ንጉሱ በራሱ ልጅ ላይ ሞት በይኗልና ህዝቡ ብርሃን ወጣልን /እውነት/ ሲል ደብረ ብርሃን ሲል ከተማዋን ሰየመ።

እናሥ? እርስዎስ? ልጅዎትም ቢሆን፣ የወለዱትም ቢሆን፣ ስጋዎትም ቢሆን በእውነት መፍረድ የለብዎትም? ሁሉንም እንደ ጥፋቱ እኩል እኩል መገሰፅ የለብዎትም? አለዚያማ ጎጠኞችን፣ ዘረኞችን እና ብሄርተኞችን እንዴት ወገንተኛና መድሎአዊ ስራ አትስሩ ብለው ሊገስፂቸውና ሊያስተምሯቸው ይችላሉ?

በእርስዎ ገለፃ በስልጣን ሺኩቻውም ውስጥ ሆነ ከኢ/ር ሀይሉ ጋር ባለመስማማት ችግር እየፈጠረ ያለው ዶ/ር ብርሃኑ ነው እንጂ የቀስተደመና ሰዎች አይደሉም። በእርስዎ አተያይ የቀስተ ደመና ሰዎች ከስልጣን ሹኩቻውና ከኢ/ር ሀይሉ ሻውል ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ውስጥ የሉበትም።

ሆኖም ይሄን አባባልዎትን የሚያፈርስብዎት አባባል በራስዎት አንደበት ነግረውናል። ዶ/ር ብርሃኑ የራሱን ቡድን እንዴት በቅስቀሳና ሎቢ ወደ ስልጣን ለመውጣት እንዴት ሁኔታዎችን እያመቻቸ እንደነበረ ይሄም መልካም እንደሆነና እርስዎም እንደሚደግፉት እንደወጣና በመጭው አምስት አመትም ወደ ስልጣን አስረድተውናል። የተመለመሉትም የዶ/ር ብርሃኑ ሰዎች በዋናነት በቀስተ ደመና መሆኑ ግልፅ ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መቼስ ፊደል ለቆጠረ ቀርቶ ገጠር ላሉ ሰዎች ይሄ አይነት የአገሞ ጠቀም ገለፃ ልባቸው እስኪፈርስ ያስቃቸዋል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በዋናነት የቀስተደመና ሰዎችን በአጋርነት የአድሊ ሰዎችን አሰልፎ ዋና ዋና የፓርቲውን የስልጣን ቦታዎች ተቆጣጥሮና ፕሬዝዳንቱ የሚወስኑትን ውሳኔዎች እየገለበጠ እስከመሻር ደርሶ ሳለ እርስዎ በዚህ ላይ ምንም ከረር ያለ ነገር ሳይናገሩ ያልፉታል፡፡

ነገሩን በማድበስበስና ልክ ዶ/ር ብርሃኑ ከኢ/ር ሀይሉ እኩል ስልጣን ያለው በማስመሰልና ሁለት እኩል ተቀናቃኝ ቡድኖች እየተሸኮቱ ለማስመሰል «አንዱ ሲሾም አንዱ ሲሺር» ብለው አስገራሚ በሆነ መልክ ይገልፁታል፡፡

ለመሆኑ ዶ/ር ብርሃኑ ኢ/ር ሀይሉ አምባገነን እርምጃ ወስደው ቢሆን እንኳን በየትኛ ው ስልጣኑ ነው እሳቸውን ውሳኔ ለመገልበጥ የሚችለው?

እርስዎ አንድም ቦታ በድፍረት ያለገለፁት እውነት ቢኖር «ዶ/ር ብርሃኑ፣ ወ/ት ብርቱካን እና ኢ/ር ግዛቸው የፕሬዝዳንቱን ስልጣን የተጋፉበት አካሄድ ህገወጥ ነበር» ብለው መመስከር አለመቻልዎ ነው፡፡

ደግሞም ኢ/ር ሀይሉ አምባገነን ሆነው አስቸግረው ከነበረ እርስዎ እንደሚሉትና (በኮሚኒስታዊ አካሄድ) ቅስቀሳና ሎቢ በማድረግ በላዕላይ ኮሚቴው እንዲወርዱ ማድረግ ይቻል ነበር፡ ግን ነገሩ የቀስተ ደመና ቡድን በግፉ በለው የያዘው ጉዳይ ሆነና እርስዋም ልጆቼ የሚሏቸውን ወጣቶች ላለማስነካት የተከላካይት ቦታ ይዘው ቁጭ አሉ፡፡

ይሄ እውነት ታዲያ በአቶ ገብረክርስትና በአቶ ታረቅኝ መፅሀፍ ውስጥ ያነበብኩትን አሳዛኝ እንድፋጠጥ አደረገኝ፡፡

«በላዕላይ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ አቶ ልደቱ ብድግ ብሎ በ60 ሰዎች ፊት እነ ፕሮፌሰር መስፍን እና ዶ/ር ብርሃኑ ኢ/ር ሀይሉን ከፕሬዝዳንትነት እናወርድልሃለን ብለውኝ ነበር፡፡ ይሄ ቃል ኪዳን ግን ተግባራዊ አልሆነልኝም» ብሎ ስብሰባውን ረግጦ የወጣበትን እውነት አስታወሰኝ፡፡

ሲጀምር እርስዎን የሚያክል ያገር ሺማግሌ እና የህሊና ልእልና ላይ ደርሻለሁ የሚል ምሁር እንዲህ አይነት ቃል ኪዳን ማስጠት ውስጥ ምን አስገባዎት? ብዙሃኑ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሰው ኢ/ር ሀይሉ ሻውል ብቃት አለው ይምራን ብሎ የሚቀጥል ቢሆን እርሶና ዶ/ር ብርሃኑ በምን ስልጣናችሁ ነው ኢ/ር ሀይሉን ከፕሬዝዳንትነት ለማውረድ የምትችሉት? በዚያችው በኮሚኒስታዊ ስልትና ስትራቴጂ መሆኑ ነው? ነው ወይስ በእርስዎ የመሸፋፈኛ አባባል በቅስቀሳና በሎቢ?

የእውነቱ ቋጠሮ ሊጎተት ወደ ጥልቁ ጓዳ ይዞን ይዘልቃል:: እርስዎ ይሄን ተንኮልና ሸር በኢ/ር ሀይሉ ላይ እንደሻረቡ ኢ/ር ሀይሉ ከአቶ ልደቱ አንደበት የሰሙ እለት በእርስዎ ላይ ያላቸው እምነት እንደጉም የተነነ ይመስላል::

እርስዎም ከዚያን ቀን ጀምሮ እነ ዶ/ር ብርሃኑ በሚጎነጉኑት የተንኮል መረብ ተተብትበው የኢ/ር ሀይሉን የፕሬዝዳንትነት መሠረት ገዝግዘው ለመጣል የተሰለፉ ይመስላል:: ሆኖም የዋሁን የኢትዮጵያን ህዝብ ለማሞኘት እርስዎ አስታራቂና ሽማግሌ መስለው ለመታየት ይፍጨረጨራሉ:: ገለልተኛ ሽማግሌ ነኝ ይሉናል:: በዚያው በሰጡት ጋዜጣዊ ቃለ መጠይቅ ላይም አቶ አባይነህ ብርሃኑ እንደተቆንዋት ገልፀውልናል:: ቅሬታዎትንም በግልፅ አስቀምጠዋል:: የእውነቱ ቋጠሮ ወደ ሌላ ጓዳ ይዞን ይዘልቃል:: አቶ አባይነህን አልወደዷቸውም:: ስለዚህም ከኢ/ር ሀይሉ ጋር የተሰለፉትን አቶ አባይነህንም ለማጥላላትና ገታራ እና ገትጋታ እንደሆኑ ለማሳየት ታጥቀው ተነሱ:: የኢትዮጵያንም ህዝብ በህሊናዎ ልዕልና የሚመራውን እውነት ሳይሆን በሰበአዊ ስሜትዎት የሚነዳውን እውነት ሊግቱት ተነሱ:: ለምን? እውነት ምንድን ነው? እያንዳንዳችን በስሜታችን የሚታየን ነገር ሁሉ እውነት ነው እንዴ? እናም በደፈናውና በጥቅሉ ልጅዎትን ቀስተደመናን ከደሙ ለማዳን ፀቡ በዶ/ር ብርሃኑና በኢ/ር ሀይሉ መሀል ነው ሲሉ ይደመድሙልናል::

ያም ሆኖ ግን በጥቂቱ ትንታኔ የሚችል ሰው ያዝንብዋታል:: ቀጥለው በተናገሩት ንግግር:: አስከትለው ሲናገሩም ፀቡ በእነ ወ/ት ብርቱካን በሚመራው ቡድን እና እዚህ የመኢአድን ቢሮ የሙጥኝ ባሉት በእነ አቶ አባይነህ መሀል እንጅ ኢ/ር ሀይሉ ሻውል ከፀቡ ውስጥ የለበትም:: እሱ መጥቶ ሁለቱን ቡድን ሊያስማማ ይችላል:: ሲሉ ሌላ ስህተት ይሰራሉ::

እነ ወ/ት ብርቱንን አሜሪካን በሄዱበት ሰዓት ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ወግነው በፕሬዝዳንቱ ላይ በማደም እና ህገወጥ በሆነ አካሄድ ያለ ፕሬዝዳንቱ ፈቃድ በርካታ ሥራዎችን ሲሰሩ መክረማቸውን እረስተውት ነው? እነ ኢ/ር ግዛቸው ሽማግሌዎቹን አውርደን በወጣት እንተካ እያሉ ፕሬዝዳንቱን ሲዘልፉ መክረማቸውን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዘንግተውት ነው? እርስዎ ለመሆኑ ይሄን አይነት ንግግርና ህገወጥ አካሄድ እንኳን ስህተትና ህገወጥ እንደነበረ ለምን መመስከርና ይሄን ጥፋት ያጠፉ ሰዎችን መገሰፅ ተሳነዎት? ቢያንስ እርስዎስ ሽማግሌ አይደሉም? ሽማግሌዎች መሰደባቸውን እንኳን ሊያወግዙት አይገባም?

እኔ ወጣት ነኝ:: ለዕርስዎ ስለሽምግልና ስራ ልሰብክለዎት አልችልም:: ሆኖም የሽምግልና ስራ የመጀመሪያው መርሁ አድሎአዊነትን ማስወገድ ነው:: እርስዎ ግን የፕሬዝዳንት ሀይሉ ሻውልን ወገን ህገወጥ እና አምባገነን እስከማለት ይዘልቁና የእነ ወ/ት ብርቱካን ቡድንን ግን ስህተቱን እያሽሞነሞኑ ያልፉለታል:: ሸፈን ሸፈን ያደርጉለታል::

የመኢአድ ሰዎች የሚሉአቸውን እያጣጣሉና እየኮነኑ ህገወጥ ለማለት ሚፈርጇቸው ቀስተደመና ግን ልጅዎት ነውና ከፀቡና ከግጭቱ ደም ንጹህ እንደሆነ ይነግሩናል:: በልብዎት ውስጥ ቀስተ ደመና አሁንም አለ:: አልሞተም:: በቅንጅት ውህደትም አልተነካም:: ሆኖም በሚያሳዝን ሁኔታ መኢአድ ከስምና ቢሮዎቹ ሁሉ ተነጥቀው በእነ ወ/ት ብርቱካን ቁጥጥር ስር ሲውል ያልማሉ:: ይሄ ምን ማለት ነው?
ፍትህ ማለት ይሄ ይሆን?

ተከታይዎችዎት እንዳይነኩቦት የፍትህን ትርጉም ማዛባት አለብዎት ማለት ይሆን? ይገርማችሁ ብለው የኢ/ር ሀይሉን እና የተከታዮቻቸውን ግንኙነት የጌታና የባህሪያ ነው ሲሉ ምስክርነት ሰጡን:: ሆኖም መገለጫ ባህሪቱን አንዱንም መጥቀስ አልቻሉም:: በአንድ ፊት ኢ/ር ሀይሉ ሻውልን እንዲህ እየዘለፉ እና እየኮነኑ በሌላ መልኩ ደግሞ ኢ/ር ሀይሉ በዚህ ፀብ ውስጥ የለበትም ሲሉ ይሰብኩናል:: የባሪና የሎሌ ግንኙነት ያሉትን ሳያብራሩልን፣ እንዴት እንደሆነም ሳይገልፁልን ብቻ ዝም ብለን እንድንአምንዎት እንዳልዎተወቱን ሁሉ መልሰው ኢ/ር ሀይሉ ይሄን በሁለት ቡድኖች መሀል ያለ ፀብ ሊፈታ የሚችል ሰው አድርገው ያቀርቡልናል:: ቀጥለውም ፀብ ውስጥ እርስዎ እንደሌሉበት ያስረዱናል:: ሽማግሌ እንደሆኑም ይነግሩናል::

ሀቁ ግን እርስዎ በአንድ ወገን ኢ/ር ሀይሉ በሌላ ወገን እከረረ ፀብ ውስጥ መግባታችሁ ነው:: በመሆኑም እርስዎን እና ኢ/ር ሀይሉ ሻውልን የሚያስታውቅ ሌላ ሶስተኛ ሽማግሌ ያስፈልጋል እንጂ እርስዎ እንደሚገልፁት እርስዎ ሽምጋይ መሆን አይችሉም:: ወይም ደግሞ ፀቡ እርስዎ እንደሚሉት የመኢአድ ቢሮን ተቆጣጥረው ባሉት ሰዎችና በእነ ወ/ት ብርቱካን መሀልም አይደለም:: ፀቡ በዋናነት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የፕሬዝዳንቱን ህልውናና መሰረት በህገወጥ አካሄድ ለመናድና ለመገርሰስ በሚደረግ ሩጫና ይሄን ላለማስነካት በሚደረግ ግብ ግብ መሀል ነው:: እዚህ አዙሪት ውስጥ እርስዎም ገብውበታል:: ስለዚህ እኔ ሽምግልና ለማድረግ ሞክሬያለሁ:: እያሉ ለምን ይነግሩናል?

4ኛ. <u>በአንድ ፓርቲ ውስጥ ሊኖር የሚገባው የስልጣን ተዋረድና የስልጣን ክፍፍልን በተመለከተ ያለዎት ፍልስፍና አገር እስከማጥፋት ሊሄድ እንደሚችል ተገንዘበውት ይሆን?</u>

ከስህተት ሁሉ ትልልቅ ስህተት ተብለው በአለም ላይ የሚጠቀሱት ስህተቶች የታላላቅ ሰዎች ስህተቶች ናቸው:: በአንድ ፓርቲ ውስጥ ሊኖር የሚገባው የሥልጣ ተዋረድና የሥልጣን ክፍፍልን በተመለከተ እርስዎ ያለዎት ፍልስፍና አገርን እስከማጥፋት ሊሄድ የሚችል መሆኑን ሳስብም እርስዎን ከሚያህል ምሁር የወጣው ስህተት ግዝፈቱ ያስፈራኛል::

እራስዎት የተናገሩትን ላስፍረው «የሥልጣን ጥምንና የሥልጣን ሽኩቻን መለየት አለብን:: በዲሞክራሲዊ ስርዓት ሁለቱ ግልፅ ናቸው:: እዚህ ጋር ባዶ ወንበር አለ:: እዚህ ወንበር ላይ ማን ይወጣል? ሚባል የስልጣን ትግል ይመጣል:: ግልፅ ትግል ነው ያ ቀላል ነው:: በአጋዛዝ ስርዓት ውስጥ የሚደረግ የስልጣን ሺኩቻ ግን ግልፅ አይደለም:: ሺፍንፍን ነው:: መጀመሪያ ነሀር ወንበር የለም:: ገና ለሚፈጠር ወንበር ነው:: ወደዚያ የሚደረስበት ተቋማዊ ስርአት ያለው መንገድ ተሰርቷል:: በቅንጅት ውስጥ ግን ያቺን እንደ ምንም አድርጎ ለማለፍና ራስን ወደፊት ለማዘጋጀት የሚደረግ ነው:: የስልጣን ጥም በውስጥ ያለ በተለያዬ መንገድ የሚገለጥ ነው:: እሱ በግልጽ ውድድር የሚታይ አይደለም:: ግልጽ ውድድርማ ግልፅ ውድድር ነው:: እዛም ውስጥ የስልጣን ጥም ቢኖርም ግልፅ የሆነ ህዝብ የሚያውቀው ውድድር አለበት:: የሥልጣን  ጥም የራስ ነው:: የግል ነው:: የብቻ ነው:: መንገድ ሲያገኝ ይወጣል:: መንገድ ሳያገኝ ታፍኖ እዛው ቁጭ ይላል:: ልዩነታቸው ይሄ ነው::» ይሉናል ፕሮፌሰሩ::

ይሄን ከላይ የተቀመጠውን ፓራግራፍ ደግሞ ቀደም ብለው በሚገርም ሁኔታ ሲገልፁት «የሥልጣን ግብግቡማ ይገለጥ የነበረው በሺኩቻ ነው:: አንዱ ያለውን አንዱ ይቃወማል:: አንዱ እሺ ያለውን ሌላው እንቢ ይላል:: አንዱ ለአንደኛው እንቅፋት እሆናለሁ ሲል ሌላውንም የማያራምድ ሆነ በአላማ ልዩነት የላቸውም

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በቅንጅት አላማ ማለቴ ነው:: ያላቸው ልዩነት አንዱን አዳክሞ ሌላውን መረማመጃ ሊያደርገው ነው:: አንዳንዶቹማ የሚያስቡት ወደኋላ ነው:: ብርሃኑ የሚያሠላው ከአምስት አመት በኋላ ስለሚመጣው ነው:: እደሚመሥለኝ የሥልጣን ሺኩቻ ሲባል ሰው የሚገባው አንድ ክፍት ቦታ እንዳለና እዚያ ላይ ለሥልጣን ግብ ግብ እንደሚደረግ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ራሳቸውን ለወደፊት እጩነት ሲያዘጋጁ ከወደፊት የሚመጣ ትግል አለ» ሲሉ ያብራሩልናል:: በዚህም የተነሳ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ለቀው እደነበረ አብረው ይገልፁልናል::

እንግዲህ ፕሮፌሰር ምን እያሉን ነው? በአንድ መልኩ በዲሞክራሲያዊ ስርዓቱ ውስጥ አንድ ክፍት ወንበር እንዳለ ሲታወቅ ለዚያ ወንበር የተለያዩ እጩዎች በግልፅ መታገላቸው አግግብ መሆኑን ሊያሳዩን ይሞክራሉ:: እንደምሳሌም ብርሃኑ ከአምስት አመት በኋላ ክፍት የሆነ ወንበር ስለሚታየው እንዴት የስልጣ ትግል ውስጥ ከወዲሁ እንደገባ፣ የራሱን ቡድን እንደ ሰበሰበና ከአቶ ልደቱና ከኢ/ር ሀይሉ ጋር ከፍተኛ ትንቅንቅ ውስጥ እንደገባ ያብራሩልን እና ይሄም በግልፅ የሚካሄድ ስለሆነ ዲሞክራሲያዊ ነው እያሉ ይሉናል::

በሌላ መልኩ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ትግል እንዴት ስራዎችን እንዳቆማቸው እና እራሳቸውም በዚህ ተማረው ስራ አስኪያጅ ኮሚቴውን እንደለቀቁ ይተርኩልናል:: ሆኖም እሳቸው የተማረሩበትን ሁኔታ ለኢ/ር ሀይሉ ሥራ እንዴት እንቅፋት እንደፈጠረባቸውና የፕሬዝዳንቱን ስራ እንዴት የእግር እሳት እንዳደረገባቸው ሊነግሩን አይፈልጉም:: ቀድመው ኢ/ር ሀይሉን ጠልተዋቸዋልና አይፈረድባቸውም:: ከዚያ ይልቅ የስልጣን ሹኩቻና የስልጣን ጥም በሚል የቃላት ማድበስበሻ ነገሩን ሊዘጋጉት ይሞክራሉ?

ለመሆኑ ዶ/ር ብርሃኑ የራሱን የመሳሳብ ቡድን ሲመሰርትና ቁልፍ ቁልፍ ስፍራዎችን ሲያሲዝ እርስዎም እርሱ የመለመሏቸውን ቡድኖች ሲያፀድቁና ብራኬ እየሰጡ ግፋ በለው ሲሉ ህዝቡ በግልፅ እያዩ በዲሞክራሲዊ መንገድ ነበር:: ወይስ በኮሚኒስታዊ አካሄድ? ለመሆኑ እርስዎና ዶ/ር ብርሃኑ ኢ/ር ሀይሉን ከፕሬዝዳንትነት እንደምታወርዱለት ለአቶ ልደቱ ቃል ስትገቡለት በግልፅ ህዝቡ እያየና ዲሞክራሲያዊ ድጋፍ እየሰጣችሁ ነበር?

ምን እያሉን ነው? በአንድ ፓርቲ ውስጥ የሥልጣን ተዋረድና የስልጣን ክፍፍል የለም ማለት ነው? ይሄ የዕዝ ሰንሰለት አይከበርም ማለት ነው? ለመሆኑ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ፕሬዝዳንቱን ተጋፍቶ ስራዎች እንዳይሰሩ የሚያደርግ፣ የራሱን ውሳኔ ሲያስተላልፋና የራሱን የመሳሳብ ቡድን ሚመሰርት እርስዎ ለምን ዶ/ር ብርሃኑን ተው አላሉትም?

እዚህ ጋር ሲደርሱ የሀበሻ ባህል ሆኖብኝ ያሉትን አባባል አልጠላሁትም። ሆኖም የሀበሻ ልብ ሆኖብዎትም የሽፈኑት ሀቅ አለ። በአንድ ፊት ስልጣን ለቀማ ነው ከሚል አካል ከሌላ በኩል ከህዝብ በሶስተኛ ወገን እነ ብርሃኑ በከፈቱባቸው የሶስትዮሽ ጫና እሣት ላይ የተቀመጡትን የፓርቲያችሁን መሪ እውነታ ለጥቂቱ እንኳን ለመግለፅ አለመፈለግዎት ያሳዝናል። ከዚያ ይልቅ ኢ/ር ሀይሉ የባሪያና የሌሎች ግንኙነት ነው የሚፈለገው ሲሉ ፕሬዝዳንቱን ተቹ።

ለመሆኑ በእርስዎ አገላለፅ መሠረት ገና ከአምስት አመት በኋላ ለሚኖር ክፍት ቦታ ብርሃኑ፣ ልደቱ፣ ኢ/ር ግዛቸው፣ እና ሌሎችም ቢሻኮቱ፣ ቢታገሉና ለዚያች ክፍት ቦታ ቢፋጠጡ በፓርቲው ውስጥ ምን ሊከሰት ይችላል? እንበልና ፓርቲው ስልጣን ቢይዝ ኖሮ እና አገር እየመራ ይሄ ፍጭትና ሽኩቻ ለዚያች ለክፍት ቦታ ቢሆን ምን ሊከሰት ይችላል?

አገር እስከ መፍረስ ሊሄድ እንደሚችል መቼም አይጠፋዎትም። መቼም የስልጣን ተዋረድና የስልጣን ክፍፍል የሚለው ጉዳይ እንደማይጠፋዎት እርግጠኛ ነኝ።
እርስዎ ከቃለ መጠይቅዎት ላይ በተዘዋዋሪ እንደመለከቱት አቶ ልደቱ ከወ/ት ብርቱካን የተሻለ ችሎታና ልምድ ቢኖረውም በቅስቀሳና በሎቢ ወ/ት ብርቱካን ልትሾም ችላለች።

የእርስዎ ዲሞክራሲ ለመሆኑ እውነት፣ ችሎታና ብቃትን ግንዛቤ ውስጥ አያስገባም እንዴ? የእናንተ ፓርቲ እንደ ፓርቲ ሊያጠነክረውና ሊመራው የሚችለውን ግለሰብ መርጦ ተገቢ ቦታ ላይ በፍትሃዊነትና በሀቅ ማስቀመጥ አይችልም እንዴ? መሪ ማግኘት እኮ አባል የመሰብሰብ ያህል ቀላል አይደለም።

አቶ ልደቱ የተሻለ የፓርቲው ተ/ቀ/ምክትል ፕሬዝዳንት መሆን ከቻለ ለምንድ ነው።
ፓርቲው እራሱ እተገቢው ቦታ የማያስቀምጠው ለምንድን ነው እሱ ቅስቀሳና ሎቢ ውስጥ የሚገባው? እንግዲያውስ ልደቱ መታቀቡ ጥሩ ነበር እላለሁ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በዲሞክራሲ በሚመሩ ሀገሮች ውስጥ ችሎታ ያለው የፓርቲ መሪ ለፓርቲው ህልውና ቁልፍ ስለሆነ በባትሪ ተፈልጎና ተጠንቶ ይገኛል:: በእኛ ሀገር ደግሞ ችሎታ ያለውን እና ልምድ ያለውን ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ ሎቢና ቅስቀሳ ይሰራበታል::

በእርስዎ ፍልስፍናም መሰረት ከአምስት አመት በኋላ ለምትኖር ክፍት ቦታ የስልጣን ሺኩቻ ዲሞክራሲያዊ በሆነና ግልፅ በሆነ መንገድ አምስት አመት ሙሉ ሰዎች ሲናቆሩ ሊዘልቁ ነው:: ዲሞክራሲ እንዲህ ለትርጉም ግራ እስኪገባ ድረስ ለእኛ ለሀበሾች ፅንሰ ሀሳቡም ተግባሩም የተሰወረን ለምን ይሆን?

በእርስዎ ፍልስፍናም መሰረት ለዚህች ከአምስት አመት ብኋላ ለምትኖር ባዶ ቦታ እነ ዶ/ር ብርሃኑ በሚፈጥሩት ግልፅ የሥልጣን ሺኩቻ እና ትግል የፓርቲው ፕሬዝዳት ፓርቲውን መምራት ተሥኖት ሺባ ይሁን?

ገና ለገና ሰዎች እራሳቸውን በእጩነት ለወደፊቱ ባዘጋጁ ቁጥር በሚፈጥሩት የሥልጣን ትግል ስራዎች ይገቱ? ለነገሩ እራስዎትም ከስራ አስኪጅ ኮሚቴው መሮዎት የወጡት ለዚህ ነው:: ግን በግልፅና በድፍረት ይህን ሁኔታ የፈጠሩት ቡድኖች እነ ዶ/ር ብርሃኑና ተከታዮቹ ስህተት ስለሰሩ ይታረሙ ከማለት ይልቅ ችግሩን የዶ/ር ብርሃኑ እና የኢ/ር ሀይሉ ጉዳይ ብቻ አድርገው አቀረቡት:: ይሄ አደገኛው ስተትዎት ነው::

ለመሆኑ ዶ/ር ብርሃኑ በምን ስልጣኑና አቅሙ ነው ከፕሬዝዳንቱ ጋር ሊገዳደር የሚችለው? እርስዎ ቡድን የለውም ብለው ሊክዱት ቢሞክሩም የዶ/ር ብርሃኑ የመተማመኛ አቅሙና ፕሬዝዳንቱን ለመገዳደር የቻለበት ብቻኛው የሀይል ምንጩ በኮሚኒስታዊ ስልት የመሰረተው ፓርቲ ነው:: ደግሞ ሌሎችን ዞሮ ከሚኒስቶችና ስታሊኒስቶች ሲል ይተቻል:: ማወቅ ይህችን ያህል መጠላለፍን ለመፍጠር ከሆነ ምን እንላለን?

## 5. ለምን አንድ ወገን እውነትን ብቻ ይገልፃሉ?

አመራሩ ከእስር እንደተፈታ ከእስር ለተፈታው አካላት ለመቋቋሚያ ተብሎ ገንዘብ መሠጠት ተጀምሮ ነበር:: ሆኖም ገንዘብ የተሰጣቸው ሰዎች ለቀስተ ደመና ሰዎች ብቻ እየተመረጡ ነበር:: የሌሎች ወገኖች አልተሰጣቸውም ነበር:: በተለይም የመኢአድ ሰዎች አምስት ሳንቲም አላገኙም ነበር:: ይሄንንም ያደረጉት እነ ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ነበሩ:: እርስዎ ግን ይሄን አንድም ቦታ ሳይገልፁ እና ፍትሃዊነትን ሳያስመሰክሩ በእርስዎና በአቶ አባይነህ ብርሃኑ መሀከል የተካሄደውን ጭቅጭቅ ብቻ አነሱት ለምን ሲባል እርስዎ ለፓርቲ አባላት አሳቢ እነ አቶ አባይነህ ደግሞ ጨካኝና ግትር ለሌላው ዴንታ የሌላቸው መሆናቸውን ለማስረገጥ የታቀደ ስልት ነው::

አሁን ገባዎት የሀበሻ ልብ ያልኩዎት? እኔ የምልዎት የሀበሻ ልብ መቼም ለሽምግልና ብቁ መሆን አይችል ይሆን? ሆኖም መደምደም አይቻልም:: ደግሞስ ፕሬዝዳንቱ ህገ ደንቡ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ተወካያቸውን መተካትን ከህግ አንፃር ሰፍቶ መተርጎም እንዳለበት እያወቁ ጠብቦ መተርጎም አለበት ከሚሉ ሰዎች ጋር ቆመው ለምን ህገወጥ ይላሉ?

**6. ለማስታረቅ ሞክረዋል? ሀላፊነትስ አለብኝ ብለው በእውነት አምነዋል?**

እንደ እርስዎ የተከበረና የታወቀ ምሁር ለፕሮፓጋዳ ብሎ ኢፍትሃዊ ወደሆነ ጎዳና ሳይኬና አንተም ተው አንተም ተው ከማለቱ በፊት እራሱን ከወገንተኛነት ቢያፀዳ መልካም ነው::

ሥህተቶች ከሁለቱም ወገን ቢሰሩም ስህቶቹን በጥንቃቄ በማጥናትና እያንዳንዱ ሥህተት ላይ ከእንዳንዱ ወገን ጋር በመሆን የለዘበ አቋም የሚያዝበትን ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት ከዚህ በኋላም ሰዎች ስለስህተቱ ሳይሆን በአብሮነት ስለሚገነው አዎንታዊ ጎን እንዲያስቡ ማበረታታትና እንቢ የሚለውን መገሰፅ ተገቢ ነው:: እርስዎ ግን ጭልጥ ብለው ወገንተኛ ሆነው ከሚያብሯቸው የኢትዮጵያ ውድ ሰው እንዲህ ዓየነት ነገር ማየት ያሳምማል::

**7. እውነት ማን በወርዷና በቁመቷ ልክ ይናገራት?**

እንደ ኢትዮጵያ በብዙ ነገር የተወጠረ ሀገር ቢያንስ ጥቂት የእውነት ሀዋርያት ቢኖሯት ሙሉ ቁስሏን ባይሆንም ጥቂት ህመሟን ሊያስታግሱላት ይችላሉ:: መቼም የተለያዩ ቡድኖችን በመደገፍ የምንቆም ሰዎች ቁጥራችን ቢበዛም ቢያንስም በዋነኛነት እና በመሰረታዊነት ግን እውነትን በወርዷና በቁመቷ ልክ በድፍረት የሚናገሩ ወገኖችን እንደማግኘት መፍትሄ የለም::

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የተከበሩ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርምም ማናዊ መሆን ያለበት አንዱን ቡድን ወግ ነው:: ሌላውን ወገን ህገወጥ፣ አምባገነን፣ ባሪያና ሎሌ ምናምን እያሉ መንቀፍ አይመስለኝም:: ይሄ የትም አያደርስም:: አንዳንድ የዋሆች ፕሮፌሰር መስፍን ከተናገሩ ህዝቡን ሁሉ ግለብጥ ብሎ ወደ እኛ ይመጣል ብለው አስበው ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ አለማወቅ ነው:: እውነቱን ለመናገር ህዝቡ ረቀቅ ያለና ሰፊ አመለካከትን መሰረት አድርጎ እየተጓዘ ያለ ህዝብ ነው::

ከአስገረሙኝ ነገሮችም አንዱ ህዝቡ ለመወሰን የማይቸኩል፣ ከስሜታዊነት የፀዳና እውነተኛው ጉዳይ ላይ እስኪደርስ ሁሉንም ወገን የሚያደምጥ ህዝብ ነው:: ሀበሻ እንደ ህዝብ ግሩም ህዝብ ሆኖ ሳለ እውነትን በወርዷና በቁመቷ ልክ ሊመሰክርለት የሚችል የሀገር ጥላ የማጣቱ ሚስጥር ግን እስካሁን ሊገለፅልኝ አልቻለም::

ሰላም ያድርገዎት!<br>ጤና ይስጥዎት!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com